# እንዲህ ብለው ነበር !



ቅንብር : አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ሰው የሚመከረው አንድም ከፊደል
አንድም ከመከራ ነው ::
አንድ ቃል ከፊደል ጥበብ ፤
አንድ ቃል ከመከራ መዝገብ ፤
አንድም በሳር « ሀ » ብሎ ፤
አንድም በአሳር « ዋ » ብሎ ::

ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን

እድሜዬን በሙሉ አልጋላይ ታስሬ፤
ታምሜ ስማቅቅ ስሰቃይ ኖሬ፤
አሳሬን ጨርሼ ይኸው ዛሬ ገና፤
እንቅልፌን አግኝቼ ማረፌ ነውና፤
የምትሄዱ በዚህ በመቃብር ቦታ፤
እንዳትቀሰቅሱኝ እለፉ በርጋታ ::

አንጋፋው ደራሲ ከበደ ሚካኤል

አጥንቱን ልቅበረው መቃብር ቆፍሬ ...
ጎበናን ከሸዋ ..አሉላን ከትግሬ ...
አገሬ ተባብራ ካረገጠች እርካብ ...
ነገሯ ሁሉ ..የእንቧይ ካብ ..የእንቧይ ካብ

ከመርሰኤ ሃዘን ግጥሞች